# ምስጢረ ቁርባን

**ጥያቄ፦ ቊርባን ማለት ምን ማለት ነው?**

ሰዎች ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት መባ ቊርባን ይባላል። ስለ ስርየተ ኃጢአት፣ ወይም ስለ ምስጋና፣ ወይም በስለት ስም ለእግዚአብሔር የሚቀርብ ነገር ሁሉ ቊር ባን ይባላል።

**ጥያቄ፦ ምስጢረ ቊርባን ማለትስ ምን ማለት ነው?**

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሰው ልጆች ኃጢያት፣ በዕለተ ዓርብ ከመሰቀሉ በፊት በዋዜማው ሐሙስ ማታ፣ ከአስራ ሁለቱ ሐዋርያት ጋር በማዕድ ተቀምጦ ሳለ ኅብስ ቱን አንስቶ ባርኮና ቀድሶ፣ ቆርሶም ለደቀ መዛሙርቱ፣ «ይህ ሥጋዬ ነው» ብሎ ሰ ጣቸው። ስለዚህ ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር፣ወይኑንም በጽዋ አድር ጎ ባርኮና ቀድሶ፣ «ይህ ደሜ ነው» ብሎ ሰጣቸው። ስለዚህ ኅብስቱ ተለውጦ ደመ ወልደ እግዚአብሔር መሆኑ ታላቅ ምስጢር ነውና ቊርባን ምስጢር መባሉ ስለዚህ ነው( ማቴ.፳፮፣፳፮፤ ማር.፲፬፣፳፪፤ ሉቃስ ፳፪፣ ፲፬-፳፫)።

**ጥያቄ፦ ምስጢረ ቊርባንን የመሠረተው ማን ነው?**

ከዚህ ከፍ ብሎ እንደ ተገለጸው፣ ምስጢረ ቊርባንን የመሠረተው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

**ጥያቄ፦ የምስጢረ ቊርባን አመሠራረት(አጀማመር) እንዴት ነው?**

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ሠላሳ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር አስተምሮ፣ እ ርሱ ራሱ ስለ ኃጢአታችን ንጹህ ቊርባን ሆኖ የሚቀርብበት ሰዓት በደረሰ ጊዜ፣ አስራ ሁለቱ ሐዋርያት ወደ ኢየሱስ ቀርበው፣ «ፋሲካን ትበላ ዘንድ ወዴት ልናሰናዳልህ ት ወዳለህ?» አሉት። እርሱም ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን ላከ፤ እንዲህም አላቸው፣«ወደ ከተማ ሂዱ፤ ማድጋ ውኃ የተሸከመ ሰውም ታገኛላችሁ፤ እርሱን ተከትላችሁ ወደሚገ ባበት ቤት ሂዱ፤ ለለቤቱ ጌታም፣ ጌታ ከደቀ መዛሙርቴ ጋር ፋሲካን የምበላበት ቤት ወዴት ነው ይልሃል በሉት፤ እርሱም በደርብ ላይ ያለውን የተነጠፈና የተሰናዳ ንጹሕና ታላቅ አዳራሽ ያሳያችኋል፤ በዚያም አሰናዱልኝ አላቸው። የተላኩትም ደቀ መዛሙር ት ወደ ከተማ ሄዱ፤ ጌታም እንዳላቸው አገኙት፤ በዚያም ፋሲካውን አሰናዱ» (ማር. ፲፬፣ ፲፪-፲፮)።

«ሰዓቱም በደረሰ ጊዜ (በመሸ ጊዜ) ጌታ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ጋር በማእድ ተቀመ ጠ፤ እንዲህም አላቸ ው ከመከራዬ በፊት ከእናንተ ጋር ይህን ፋሲካ ልበላ እጅግ እመ ኝ ነበር፤ ነገር ግን በእውነት እላችኋለሁ ፤ በእግዚአብሔር መንግሥት እስኪፈጸም ድ ረስ ወደፊት ከዚህ አልበላም አላቸው። ጽዋውንም ተቀበለ፤ አመስግኖም፤ ይህን እን ካችሁ በመካከላችሁ ተካፈሉት እላችኋለሁ፤ በእግዚአብሔር መንግሥት እንደ ገና እ ስክጠጣው ድረስ፣ ከአሁን ጀምሮ ከዚህ የወይን ፍሬ አልጠጣም አላቸው።
ከዚህ በኋላ ኅብስቱን አንስቶ አመሰገነ፤ ቆርሶም ሰጣቸውና፣ ስለ እናንተና ስለ ብዙዎች ቤዛ የሚሰጠው ሥጋዬ ይህ ነውና ብሉት፤ ይህንንም ለመታሰቢያዬ አድርጉት

(ወከመዝ ግብሩ ተዝካርየ) አላቸው። እንዲሁም ራት ከበሉ በኋላ፣ ጽዋውን አንስቶ፣ ይህ ጽዋ ስለ እናንተ የሚፈሰው ሐዲስ ኪዳን የሚሆን ደሜ ነውና ጠጡት አላቸው»(ማቴ. ፳፮ ፣፲፯ - ፳፱፤ ማር.፲፬፣ ፲፪ - ፳፭፤ ሉቃ.፳፪፣ ፯ - ፳፩)።

ከዚህ በላይ በተገለጸው መሠረት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምስጢረ ቊርባን የመሠረተ ው በዚህ መልክ ነበር። በተለይ በሉቃስ ፳፪፣፲፯ እንደ ተመለከተው፣ጌታ ከሁሉ በፊት ፣ «ጸዋውን አንስቶ አመስግኖ ሰጣቸው» ተብሎ የተጠቀሰው፣ በፋሲካው ሥርዓት መሠ

ረት በመጀመሪያ የሚቀርበውና የሚጠጣው ወይን ነበር፤ ስለዚህ ያንን ሥርዓት በመከተል፣ ጌታ የኦሪቱን የፋሲካ ማዕድ አስቀድሞ፣ የሐዲስ ኪዳን መሠረት የሆነውን ምስጢረ ቍርባንን መሥርቶ ለሐዋርያት እንደ ሰጣቸው ያመለክታል።

**<u>ጥያቄ</u>፦ቅዱሳን ሐዋርያት ከጌታ እጅ የተቀበሉት የጌታ ሥጋና ደም ኅብስቱ ሥጋ አምላክ፣ ወይኑ ደመ አምላክ ሆኖ የተለወጠው ምን ጊዜ ነው?**

ጌታችን ኅብስቱን አንስቶ በባረከውና በቀደሰው ጊዜ፣ ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ አምላክ ሆኖአል፤ ወይኑንም በጽዋ አድርጎ በባረከውና በቀደሰው ጊዜ፣ ወይኑ ተለውጦ ደመ አምላክ ሆኖአል።

**<u>ጥያቄ፦</u> በአሁኑ ዘመንስ ቀሳውስት ኅብስቱን በጻሕል፣ ወይኑን በጽዋ አድርገው የሚያቀርቡት ቍርባን የሚለወጠው ምን ጊዜ ነው?**

ኅብስቱ ሥጋ አምላክ፣ ወይኑም ደመ አምላክ ለመሆን የሚለወጠው ቄሱ፣ «አእኰተ፣ ባረከ፤ ወቀደሰ» ብሎ በባረከው ጊዜ፣ መንፈስ ቅዱስ ኅብስቱን ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር (ሥጋ አምላክ) ወይኑንም ደመወልደ እግዚአብሔር (ደመ አምላክ)፣ አድርጎ ይለውጠዋል፤ በዚህ ጊዜ ፍጹም ሥጋ አምላክ፣ ፍጹም ደመ አምላክ ይሆናል።

በ፬፻፺ ዓ.ም. በግፍና በስደት ያረፈው ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ «ይህ ሥጋዬ ነው፤ ይህ ደሜ ነው» የተባለው ቃል ስገልጽ፣ ቍርባኑ ሥጋ አምላክና ደመ አምላክ ወደ መሆን ይለወጣል ሲል እንደሚከተለው ጽፎአል፤ «ወይቤ እግዚእነ ዝውእቱ ሥጋየ፣ ዛቲ ቃል ትዌልጥ ቍርባነ ዘንቡር፣ ወበከመ ይእቲ ቃል ዘይቤ በውስተ ኦሪት ብዝኁ ወተባዝኁ ወምልእዋ ለምድር፣ ይቤ ምእረ ወኮነ ይገብር ውስተ ፍጥረት ትዝምዳተ ወትውልዳተ።

ከማሁ ዝንቱ ቃል ዘይቤ ምእረ ወውእቱ ቃል ይፈጽም ኵሎ መስዋዕተ ዘንቡር ውስተ ኵሉ ቤተክርስቲያን»፤ «በኦሪት አምላካችን፣ ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት ብሎ አንድ ጊዜ በተናገረው ቃል፣ በኣለም የሚገኙ ፍጥረታት ሁሉ ሲዋለዱና ሲራቡ እንደሚኖሩ፣ አሁንም እንደዚሁ ይህ ሥጋዬ ነው፤ ይህ ደሜ ነው ብሎ ነው ብሎ የተናገረው ቃል፣ በታቦት ላይ የሚቀመጠውና በየቤተ ክርስቲያኑ ዘወትር የሚቀርበውን መስዋዕት፣ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ደመ ወልደ እግዚአብሔር ወደ መሆን ይለውጠዋል» ሲልጽፎአል (መጽሐፈ ግብረ ህማማት ዘሐሙስ፣ ገጽ ፻፺፪)።

**<u>ጥያቄ</u>፦«አሐዱ አብ ቅዱስ፣ አሐዱ ወልድ ቅዱስ፣አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ» ከተባለ በኋላ ይለወጣል የሚሉ አሉ፤ ታዲያ ይህ ልክ ነው?**

«አሐዱ አብ ቅዱስ፣ አሐዱ ወልድ ቅዱስ፣ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ» የሚለው ጸሎት፣ የጸሎተ ቅዳሴ የመጀመሪያው ክፍል ነው። ከጸሎተ ቅዳሴው መጀመሪያ አንስቶ፣«ባረከ ወቀደሰ» ይረስዮ....እስከሚለው ድረስ ለቍርባን የመለወጫ ጸሎት ነውና በዚህ ረገድ ከሆነ ግን፣ ጸሎተ ቅዳሴው ይመሰክርባቸዋልና አባባሉ ትክክል አይደለም።

**<u>ጥያቄ፦</u> የምስጢረ ቍርባን ታሪካውያን ምሳሌዎች ምንና ምን ናቸው?**

፩ኛ. ጻድቁ አቤል ለእግዚአብሔር ያቀረበው መስዋዕተ ቍርባን፣ ጌታችን ለመሠረተው ቅዱስ ቍርባን፣ ምሳሌ ነው(ዘፍ.፬:፬)፤
፪ኛ. ጻድቁ ኖህ ለእግዚአብሔር ያቀረበው መስዋዕተ ቍርባን፣ ለአማናዊው ምስጢረ ቍርባን ምሳሌ ነው፤ (ዘፍ.፰:፳-፳፪)፤
፫ኛ. የሳሌም ንጉሥና የልዑል እግዚአብሔር ካህን መልከ ጼዴቅ፣ ለአብርሃም ያቀረበለት የተባረከ ኅብስትና የተቀደሰ ወይን፣ ጌታችን ሐሙስ ማታ ለመሠረተው ምስጢረ ቍርባን ዓይነተኛው ምሳሌ ነው (ዘፍ.፲፬:፲፰-፳)፤
፬ኛ. የአብርሃም መስዋዕትና የእስራኤል ልጆች የተመገቡት የፋሲካው በግ፣ ለአማናዊው የጌታችን ሥጋና ደም ታሪካውያን ምሳሌዎች ናቸው (ዘፍ.፳፪:፱-፲፬ ፤ ዘጸ.፲፪:፩-፳፰)።

**<u>ጥያቄ፦</u> ቅዱስ ቊርባን የሚዘጋጀው ከምንድን ነው?**

ቅዱስ ቊርባን የሚዘጋጀው ከንጹሕ ስንዴና ከንጹሕ ወይን ነው። ከንጹሕ ስንዴና ከ ንጹሕ ወይን ያልተዘጋጀ ነገር፣ በምንም አይነት ቅዱስ ቊርባን ሊሆን አይችልም። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን ሕግ (ቀኖና) እንዲህ ሲል ያስጠነቅቃል፤ «ንጹሕ ከሆነ ስን ዴ፣ ንጹሕ ከሆነም ወይን በቀር፣ ሌላ በቤተ ክርስቲያን አይሠው» (ጴጥ.ረሰጠጅ.፫፡ ፍትህ መንፈሳዊ፣ ገጽ ፪፴፰)።

**<u>ጥያቄ፦</u> ቅዱስ ቊርባን መቀበል ለምን ይጠቅማል?**

ከክርስቶስ ጋር አንድ ለመሆንና ዘላለማዊውን ሕይወት ለመውረስ ይጠቅማል። ስለዚ ሁም ጌታችን፣ «እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ የሰውን ልጅ ሥጋ (የክርስቶስን ሥጋ ) ካልበላችሁ፣ ደሙንም ካልጠጣችሁ፣ የዘላለም ሕይወት የላችሁም። ሥጋዬን የሚ በላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፤ እኔም በመጨረሻ ቀን አስነሣዋለሁ ። ሥጋዬ እውነተኛ መብል፣ ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና።ሥጋዬን የሚበላ፣ ደ ሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል፤ እኔም በእርሱ እኖራለሁ» ሲል ጌታ አስተምሮአል ( ዮሐ. ፮፡ ፶፫-፶፯)።

**<u>ጥያቄ፦</u>የጌታችን ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ የሆነውን ቅዱስ ቊርባን ከመቀበላች ን በፊት ምን ማድረግ ይገባናል?**

ሥጋውን ደሙን ከመቀበላችን በፊት፣ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ግዴታዎች መፈጸም ይገባና ል።

፩ኛ. ጸሎተ ቅዳሴውን የሚያከናውነው ካህን ኅብስቱን በጻሕል፣ ወይኑን በጽዋዕ አድርጎ እየባረ ከ፣ ጸሎተ ቅዳሴውን ሲያደርስበት፣ ኅብስቱ ተለውጦ የወልደ እግዚአብሔር ደም እንደሚሆን ከልብ ማመን ይገባል፤

፪ኛ. በሐሳብ፣ በቃል፣ በተግባር የፈጸሙትን ኃጢአት ለንስሐ አባት መንገር (መናዘዝ) ይገባል፤

፫ኛ. የሠሩትን ኃጢአት ተናዝዞ፣ ከንስሐ አባት የሚሰጠውን ቀኖና ማለትም ጾም፣ ጸሎት፣ ስግ ደት፣ ምጽዋትና ሌላም ይህንን የመሰለውን ሁሉ ተቀብሎ መፈጸም ይገባል፤

፬ኛ. ከማንኛውም ኃጢአት መራቅ ያስፈልጋል፤

፭ኛ. ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ሌላ፣ ቅዱስ ቊርባን ከመቀበላችን በፊት፣ ከአሥራ አምስት ሰ ዓት ላላነሰ ጊዜ መጾም ይገባናል። እንዲሁም ሰውነታችንን፣ ልብሳችንን አጥበንና አጽድተን ሥጋውን ደሙን መቀበል ይገባናል፤ ይህንን ፈጽመን ከቀረብን፣ ስርየተ ኃጢአትን እንቀበላለን ፤ ዘላለማዊ ሕይወትንም እንወርሳለን፤ የመንግሥተ ሰማያት ወራሾችም እንሆናለን።

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን መንፈሳዊ ግዴታዎች ሳይፈጽሙ በድፍረት፣ ምን አለበት በማለት ቢ ቆርቡ ግን፣ በራስ ፈርዶ መቀሥፍና ገሃነመ እሳት መግባት ነው። ንስሐ ሳይገቡ፣ በንስሐም ከ ሠሩት ኃጢአት ሳይናዘዙና ሳይነጹ በድፍረት ሥጋውን ደሙን መቀበል፣ የሥጋን መቅሠፍትና የነፍስንም ፍዳ የሚያስከትል መሆኑን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ምእመናን በጻ ፈው መልእክቱ እንዲህ ይላል፤ «ሳይገባው ይህን ኅብስት የበላ፣ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁ ሉ፣ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት፤ ስለዚህ ሰው ራሱን ይመርምር፤ ከዚያም ከኅብስቱ ይብላ ፤ ከጽዋውም ይጠጣ። የጌታ ሥጋ መሆኑ ሳይገባው (ሳይበቃ ወይም ብቁ ሳይሆን) የሚበላና ጽ ዋውን የሚጠጣ ለራሱ መቅሠፍትና ፍርድን(ኩነኔን) ይበላል፤ ይጠጣልም» (፩ቆሮ. ፲፩፡ ፳፯ - ፴)።

በሥርዓተ ቅዳሴው፤ ዘወትር በካህኑ አንደበት የሚታወጀው ትእዛዝ፣ «ንጹሕ የሆነ ከቊርባኑ ይቀበል፤ ንጹሕ ያልሆነ ግን አይቀበል፤ ለሰይጣንና ለሰራዊቱ በተዘጋጀው እሳተ ገሃነም እንዳ ይቃጠል። በልቡናውቂምን የያዘ፣ ልዩ ሐሳብና ዝሙትም ያለበት ቢሆን አይቅረብ» የሚል ነ ው። እዚህ ላይ «ንጹሕ የሆነ» ያለው ንስሐ የገባና የተናዘዘ ማለቱ ነው።«ንጹሕ ያልሆነ» ያለ ው ንስሐ ያልገባና ያልተናዘዘ ማለቱ ነው።
(ሥርዓተ ቅዳሴ፣ ቁ.፵፮)።

**<u>ጥያቄ፡-</u> መቁረብ የሚገባው ምን ጊዜ ነው?**

ከተቻለ በየሳምንቱ እሑድና በታላላቅ በዓላት መቁረብ ይገባል። ይህ ካልተቻለም በየአርባ ቀኑ ሥጋውን ደሙን መቀበል ተገቢ ነው፤ በተለይም በልደት፣ በጥምቀት፣ በጸሎተ ሐሙስ፣ በበዓለ ትንሣኤና በዘመነ ትንሣኤ፣ በደብረ ታቦር ሥጋውን ደሙን መቀበል ተገቢ ነው።

**<u>ጥያቄ፡-</u>ቅዱስ ቊርባን ካህኑ የቅዳሴውን ጸሎት ሳይጸልይበት በፊት በምን ደረጃ ነው የሚገኘው?**

ቊርባን፣ ጸሎተ ቅዳሴ ሳይጸለይበት ተራ ኅብስትና ተራ ወይን ነው፤ ነገር ግን ቀደም ብለን እንደገለጽነው፣ ካህኑ ኅብስቱን በጻሕል፣ ወይኑንም በጽዋ አድርጎ እየባረከ ጸሎተ ቅዳሴውን ሲያደርስበት፣ ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ አምላክ ይሆናል፤ ወይኑም ተለውጦ ደመ አምላክ ይሆናል ።

ይህንን በሚመለከት የእስክንድርያው ሊቀ  ጳጳሳት አትናቴዎስ እንዲህ ሲል ጽፎአል፤ «ዳግመኛም ሕይወትን የሚሰጥ፣ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም በሚሆን፣ በቅዱስ ቊርባንእናምናለን። ቄሱ ሳይባርከው ኅብስትና ወይን ነው። ቄሰሱ ከባረከው በኋላ ግን በላዩ ላይ መንፈስ ቅዱስይወርዳል፤ ከዚያም ኅብስት ከመሆን የወልደ እግዚአብሔርን አማናዊ ሥጋ ወደ መሆን ይለወጣል፤ ወይኑም እንዲሁ ወይን ከመሆን የወልደ እግዚአብሔር ደም ወደ መሆን ይለወጣል (ሃይማኖተ አበው አትናቴዎስ፣ ገጽ፹፮፣ቊ.፳፪)።

**<u>ጥያቄ፡-</u>መስዋዕት ማለት ምን ማለት ነው?**

ቊርባን ማለት ለእግዚአብሔር የሚቀርብ መባ ስጦታ ማለት እንደሆነ ሁሉ፣ መስዋዕት ማለትም ስለ   ኃጢአት ስለ በደል ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት የሚሰውት መስዋዕት ነው። የአቤል መስዋዕትና የኖህ   መስዋዕት በዘመነ ብሉይ ከበግ የተዘጋጀ መስዋዕት ለእግዚአብሔር መቅረብ የሚገባው መሆኑን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች ናቸው (ዘፍ.፬፡፬ ፤ ዘጸ.፳፡፳-፳፪)።

አቤል ከበጎቹ መካከል ንጹሑንና ያማረውን በግ መርጦ ለእግዚአብሔር ያቀረበው ቊርባን መሥዋዕት ይባላል (ዘፍ. ፬፡፬)። ጻድቁ ኖህም ከንጹሕ እንስሳ መካከል መርጦ ስለ ምስጋና ለእግዚአብሔር ያቀረበው የእርድ ቊርባን መሥዋዕት ይባላል (ዘፍ.፳ ፤ ፳-፳፪)።
የእግዚአብሔር ወዳጅ አብርሃም፣ በልጁ ፈንታ እግዚአብሔር የሰጠውን በግ አርዶ ለእግዚአብሔር ያቀረበው የእርድ ቊርባን መሥዋዕት ይባላል (ዘፍ. ፳፪፡ ፲፫-፲፬)።

በኦሪት ዘሌዋውያን በሰፊው እንደተገለጸው፣ የእስራኤል ልጆች በእግዚአብሔር ትእዛዝ ስለ ኃጢአታቸውሥርየትን፣ ስለ በደላቸው ይቅርታን ለማግኘት ልዩ ልዩ መሥዋዕት፣ ማለት የደህንነት መሥዋዕት፣ የበደል መሥዋዕት፣ የምስጋና መሥዋዕት፣ በእሳት የሚቃጠል ጣፋጭ ሽታ ያለው፣ ከእህል ወይም ከእንስሳ የሚቀርብ መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ያቀርቡ ነበር (ዘሌ.፩-፲)።

**<u>ጥያቄ፡-</u> አማናዊው (እውነተኛው) መሥዋዕት ማን ነው?**

የሰዎችን ኃጢአት የሚያስወግድ እውነተኛው መሥዋዕት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱም ራሱንያማረና የተወደደ መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር አብ ያቀረበ፣ እውነተኛ የዓለም ቤዛ ነው። ጌታችንኢየሱስ ክርስቶስ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ፣ ነውርና ነቀፋ የሌለበት፣ ንጹህ በግ መሆኑን ዮሐንስ መጥምቅ ሲመሰክር፣ «እነሆ የዓለሙን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» ብሎአል (ዮሐ.፩፡ ፳፱)።

ሐዋርያው ጴጥሮስም፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ንጹህና ነውር እንደ ሌለበት በግ መሥዋዕት ሆኖ በክቡር ደሙ የሰውን ልጆች እንደ ዋጀ መስክሮአል፤ «ከአባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከከንቱ ኑሮአችሁ፣ በሚያልፍና በሚጠፉ ነገር በብር ወይም በወርቅ ሳይሆን፣ ነውርና ነቀፋ በሌለበት እንደ ንጹህ በግ ደም፣ በክቡር የክርስቶስ ደም እንደ ዋጃችሁ ታውቃላችሁ» (፩ጴጥ. ፩፡ ፲፰-፳፩)። ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም፣ «ወደሙ ለኢየሱስ ክርስቶስ ያነጽሐነ እምኲሉ ኃጣውኢነ»፤ (የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል» ሲል መስክሮአል (፩ዮሐ. ፩፡ ፯)።

**<u>ጥያቄ፡-</u>በዘመነ ብሉይ ሰዎች ለእግዚአብሔር ያቀርቡት የነበረው የእንስሳት መሥዋዕትና  የእንስሳት ደም፣ ኃጢአትን ለማስወገድ ይችል ነበርን?**

በዘመነ ኦሪትና በዘመነ ነቢያት ከኮርማዎች፣ ከበጎች፣ ከፍየሎች ይቀርቡ የነበሩት መሥዋዕቶች የሥጋን ርኩሰትና ነውርን ለማስወገድ የሚችሉ እንደነበሩ የታወቀ ቢሆንም፣ የነፍስን ርኩሰ

ትና በደልን፣ (ኃጢአትን) ማስወገድ አይችሉም ነበር። ምክንያቱም፣ ኦሪት(ሕገ ኦሪት) በአዳም ስሕተት ምክንያት ወደ ዓለም የገባውን ሞት (ሞተ ኃጢአትን) ማስወገድ እንዳልቻለች፣ የኦሪት መሥዋዕትም ሥርየተ ነፍስን ማሰጠት አልቻለም። «ወሶበ ተስእኖ ለሕገ ኦሪት ሳዕለ ሞት በእንተ ድካመ ሥጋ፣ ፈነወ እግዚአብሔር ወልዶ በአምስለ ነፍስተ ኃጢአት፣ ወኰነና ለይእቲ ኃጢአት በነፍሳቱ» ሲል ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ያስተማረውስለዚህ ነው። ይህም፣ «ከሥጋ ድክመት የተነሳ፣ ሕገ ኦሪት በሞት ላይ የአሸናፊነት ሥልጣን በማጣቱ፣ እግዚአብሄር ልጁን በኃጢአተኛው ስጋ ምሳሌ (እንደ ኃጢአተኛ ሰው ሆኖ) ኃጢአትን በስጋው አጠፋት»ማለት ነው (ሮሜ፰፡ ፫-፬)። በሌላ ክፍልም የኦሪት መሥዋዕቶችና ሥርዓቶች በሙሉ በዘመነ ሐዲስ ለተፈጸመው አማናዊው መሥዋዕት ምሳሌዎች መሆናቸውን በመግለጽ ሐዋርያው እንዲህ ብሎአል፤«እነዚህም እስከ መታደስ ዘመን ድረስ የተደረጉ፣ ስለ ምግብና ስለ መጠጥ ስለ ልዩ ልዩ መታጠብም የሚሆኑ የሥጋ ሥርዓቶች ብቻ ናቸው» (ዕብ. ፱፡፲)።

በየጊዜው ይቀርብ የነበረው የእንስሳት መሥዋዕት፣ በሰው ልጆች ላይ የሰፈነውን ኃጢአት ሊያስወግድ  አለመቻሉን በመግለጽ፣ ይኸው ሐዋርያ ሲያስተምር፣ «ቦሙ ዘይገብሩ ተዝካረ ኃጢአት በበዓመት፤ እስመ ኢይክል ደመ ላህም ወጠሊ ይኅድግ ኃጢአት»፣ «በዚያው መሥዋዕት በየዓመቱ የሚቀርብ የኃጢአት መታሰቢያ የነበራቸው፤ የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ኃጢአትን ማስወገድ(ማስተስረይ) የማይችል ነውና» ብሎአል (ዕብ.፲ ፡፫-፭)።

የኮርማዎችና፣ የፍየሎች የበጎች መሥዋዕት ኃጢአትን ማስወገድና በደልንም መደምሰስ የማይችል በመሆኑ፤  የተወደደና የሰመረ መሥዋዕት ሆኖ በክቡር ደሙ የዓለምን ኃጢአት ያስወግድ ዘንድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ዓለም እንደሚመጣ አስቀድሞ እንዲህ የሚል ትንቢት ተናግሮ ነበር፤ (መሥዋዕትንና መባን (ቍርባንን) አልወደድህም፤ ሥጋን አዘጋጀህልኝ፤ በሙሉ በሚቃጠል መሥዋዕትና ስለ ኃጢአት በሚሰዋው መሥዋዕት ደስ አልተሰኘህም፤ በዚያን ጊዜ እነሆ በመጽሐፍ እራስ ላይ እንደ ተጻፈ አምላኬ ሆይ፣ፈቃድህን ላደርግ (ፍቃድህን ለመናገር) መጣሁ፣ (ወደድሁ)»። በግእዙ ግን፣ (መሥዋዕተ ዘበእንተ ኃጢአት ኢሰመርኩ፤ ውእተ ጊዜ እቤ ነየ መጻእኩ፤ ውስተ ርእሰ መጽሐፍ ተጽሕፈ በእንቲአየ፤ ከመ እንግር ፈቃደከ መከርኩ አምላኪየ» ይላል (መዝ.፴፱(፵)፮-፰)።

## <u>**ጥያቄ፦**</u>ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ንጹህና የተወደደ መሥዋዕት አድርጎ ያቀረበው መቼና ስንት ጊዜ ነው?

የዓለሙን ኃጢአት ለማስወገድ ጌታችን ራሱን የተወደደና የሠመረ መሥዋዕት አድርጎ ያቀረበው በዕለተ ዓርብ በፈቃዱ በተሰቀለ ጊዜ ነው። በዚያን ራሱን የተወደደና የሠመረ መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር አብ በማቅረብ አንድ ጊዜ ብቻ ተሰውቶአል። ጌታችን ራሱን ንጹህና የተወደደና የሠመረ መሥዋዕት አድርጎ በማቅረብ የዓለምን ኃጢአት አስወግዶአል።

«አሁን ግን በመጨረሻው ጊዜ ኃጢአትን ይሽራት ዘንድ አንድ ጊዜ ራሱን ሰዋ እንጂ ለሰው አንድ ጊዜ ሞት እንደሚቆየው፣ በኋላም ፍርድ እንደሚጠብቀው፣ እንዲሁም ክርስቶስ የብዙዎችን ኃጢአት ያስተሰርይ ዘንድ ራሱን አንድ ጊዜ ሰዋ፤ በኋላም ያድናቸው ዘንድ ተስፋ ለሚያደርጉት ኃጢአታቸውን ይቅር ብሎ ይገለጥላቸዋል» ሲል ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አስረድቶአል (ዕብ.፱ ፡፳፮-፳፰)።

አምላክ ወልደ አምላክ ክርስቶስ እርሱ ራሱ ምንም ዓይነት በደልና ኃጢአት ሳይኖርበት፣ ስለ ሰው ልጆች ኃጢአት፣ መሥዋዕት ሆኖ በመቅረብ የዓለምን ኃጢአት እንደሚያስወግድ፣ ነቢያት በዘመናቸው በመንፈስ ቅዱስ እየተመሩ ትንቢት ተናግረዋል። በተለይም ጌታችን ስለ ሰው ሁሉ መሥዋዕት ሆኖ እንደሚቀርብና የሰዎችን በደልና ኃጢአታቸውን በፈቃዱ እንደሚሸከም ፣ በፈቃዱ ስለ ኃጢአተኞች እንደሚገረፍ፣ መከራን እንደሚቀበል፣ በቁስሉም የዓለሙን የኃጢአት ቁስል እንደሚያድን ነቢዩ ኢሳይያስ በትንቢቱ አረጋግጦ ነበር (ኢሳ.፶፫ ፡፬-፲፪)።

ትንቢቱ ከተፈጸመ በኋላም፣ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በክርስቶስ ላመኑት ምእመናም በጻፈው መልእክቱእንዲህ ብሎአል፤ «ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሎአልና። እርሱ ኃጢአት አላደረገ፣ ተንኮልም በአፉ አልተገኘም፤ ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም፣ መከራንም ሲቀበል አልዛተም፤ ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው (ለእግዚአብሔር አብ) ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤ እኛ ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር፤ እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በመስቀል ተሸከመ፤በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ።እንደ በጎች ትቅበዘበዙ ነበር፤ አሁን ግን ወደ ነፍሳችሁ እረኛና ጠባቂ ተመልሳችኋልና» (፩ጴጥ.፪ ፡፳፩-፳፭) ።

**<u>ጥያቄ</u>፦ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለምን ኃጢአት ለማስወገድ ራሱን መሥዋዕት አ ድርጎ ያቀረበው ለማን ነው?**

የዓለምን ኃጢአት ለማስወገድ፣ ጌታችን ራሱን የተወደደና የሠመረ መሥዋዕት አድርጎ ያቀረበ ው ለእግዚአብሔር አብ ነው። እንዲህ ማለት ግን ጌታችን ራሱ እግዚአብሔር አይደለም ማለ ት አይደለም፤
ነገር ግን የባህርይ አምላክ ነው እንጂ፤ መሥዋዕት ሆኖ መቅረቡ ግን በሥጋው ነው። ጌታችን ከኃጢአት በቀር ሥጋን በመልበሱና ፍጹም ሰውም በመሆኑ፣ ኃጢአትን ይሽር ዘንድ በለበሰው ሥጋ በመስቀል ተሰቅሎ ሞትን ቀመሰ፤ በሞቱም ሞትን አጠፋ። በሔዋን ምክንያት ተዘግቶ የ ነበረው የሕይወት መንገድ በእርሱ (በክርስቶስ) ተከፈተልን። «እስመ ሐደሰ ለነ ፍኖተ ጽድቅ ወሕይወት ግብተ በመንጦላዕተ ሥጋሁ። ካህን ዐቢይ ለቤተ እግዚአብሔር» ሲል ሐዋርያው ያ ስተማረው ስለዚህ ነው። ይኸውም፣ «የእግዚአብሔርቤት ታላቅ ካህን የሆነው በሥጋው የሕይ ወትን መንገድ አደሰልን» ማለት ነው (ዕብ.፲ ፡፳፩-፳፪)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ እንደ መሆኑ መሥዋዕት ይቀበላል፤ ከኃጢአት በቀ ር ፍጹም ሰው እንደ መሆኑ ደግሞ፣ ሞተ ኃጢአትን ይሽር ዘንድ ራሱን የተወደደና የሠመረ መሥዋዕት አድርጎ አቅርቦአል። ስለዚህ ታላቅ ምስጢር ብዙ የቤተክርስቲያን ሊቃውንት ሰፋ ያለ ትምህርት ሰጥተውበታል። ለምሳሌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ዘኑሲስ «የሚሠዋ በግ እርሱ ነው፤ የ ሚሠዋውም ካህን እርሱ ነው። ከባሕርይ አባቱ ከአብ፣ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስም ጋር መስዋዕት የሚቀበል እርሱ ነው» ሲል አስረድቶአል። (ሃይማኖተ አበው ገጽ ፺፳፮)።

**<u>ጥያቄ</u>፦ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ እንደ መሆኑ መሥዋዕት ተቀባይ ነው፤ ፍጹም ሰው እንደ መሆኑ ደግሞ የዓለምን ራሱን የተወደደ መሥዋዕት አድርጎ በማቅረብ የዓለምን ኃጢአት ማስወገዱ የታመነ ነው፤ ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ከንጹሕ ስንዴና ከንጹሕ ፍሬ ወይን እየተዘጋጀ የሚቀርበው ቍርባን ጌታችን በዕለተ ሐሙስ ለቅዱሳን ሐዋርያት ከሰጣቸው ቅዱስ ቍርባን ጋር አ ንድ ነውን?**

ቅዱሳን ሐዋርያት በዕለተ ሐሙስ ከጌታችን እጅ የተቀበሉት ቅዱስ ቁርባንና እስከ ዕለተ ምጽ አት በቤተክርስቲያን የሚሠዋው መሥዋዕት አንድ ነው። የዚያን ጊዜ ሐዋርያት የተቀበሉት ቅ ዱስ ቍርባን፤ ዛሬም የቤተክርስቲያኑ በካህኑ አማካይነት ለምእመናን የሚሰጠው ቅዱስ ቍርባ ን ፍጹም የጌታችን ሥጋና ደም ነው።

ይህን አስመልክቶ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ስለ ቅዱስ ቍርባን በጻፈው ሐተታ ላይ፤ «ወይእቲ መሥዋዕትን ጽሕት እንተ ይእዜ ያበውኡ ካህናት፤ ወለሊሃ ይእቲ ዘተሠዐት በቀራንዮ» ፤ «ዛ ሬ በየጊዜው ካህናትየሚያቀርቧት ንጽሕት መሥዋዕት ያን ጊዜ በቀራንዮ በመልዕልተ መስቀል የተሰዋች መሥዋዕት ናት» ሲልመስክሮአል። ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያም፣ ንስጥሮስን በ መቃወም በጻፈው በአሥራ አንደኛው ውግዘቱ እንዲህ ብሏል፤ «እኛ በቤተክርስቲያን የምናቀር በው ነውርና ነቀፋ የሌለበት ፣ ሕይወት የሚያድልይህ ቅዱስ መሥዋዕት ነው፤ በቤተክርስቲያን የተዘጋጀ እኛ የምንሠዋው ይህ መሥዋዕት እንደኛ ያለ ዕሩቅ ብእሲ (የፍጡር ሰው) ሥጋ እን ዳይደለ፤ የእግዚአብሔር ቃል ሥጋ እንደ ኾነ እናምናለን፤ እንዲሁም እኛ የምንቀበለው ክቡር ደም እግዚአብሔር ወልድ የነሣው ደም ነው፤ ሁሉም ሕይወትን የሚያድል ነው» (ሃይማኖተ አበው ገጽ 574 ቁ 39)።

**<u>ጥያቄ</u>፦ቅዱስ ቍርባን ምሳሌና መታሰቢያ ነው እንጂ በእውነት የጌታችን ሥጋን ደም አይደለም የሚሉ መናፍቃን (ከሐድያን) እንደ ነበሩና በዘመናችን እንዳሉ ይታ ወቃል፤ እነዚህን በምን ዓይነት መልስ ማሳፈር ይገባል?**

እነዚህንና እነዚህና የመሰሉትን መናፍቃና እሱ ጌታችን በተናገረው ቃል ማሳፈረር ይገባል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጸሎተ ሐሙስ ማታ ከራት በኋላ፣ ምስጢረ ቍርባንን ለሐዋርያት ሲያሳያቸው ኅብስቱን አንስቶ፣ ባርኮና ቀድሶ፣ «ይህ ሥጋዬ ነው» ብሎ ቆርሶ ሰጣቸው እንጂ ፣ ይህ ኅብስት የኔ መታሰብያ ነው፤ ወይም «የሥጋዬ መታሰቢያ ነው» ብሎ አልሰጣቸውም። ጽዋውንም አንስቶ፣ አመስግኖ፣ ባርኮና ቀድሶ፣ «ስለ እናንተ ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ፣ የአ ዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነውና ከእርሱ ጠጡ» ብሎ ሰጣቸው እንጂ፣ «የደሜ መታሰቢያ ነው» ብሎ አልሰጣቸውም (ማቴ.፳፮:፳፮፤ ማር.፲፬፡ ፳፪-፳፭፤ ሉቃስ.፳፪፡ ፲፬ -፳፩)።

ስለዚህ በኅብስትና በወይን አርአያ የሚቀርበው ቅዱስ ቊርባን፣ የጌታችን ፍጹም ሥጋና ፍጹ ም ደም መሆኑን ረስተው ወይም ክደው፣ «መታሰቢያ ነው» የሚሉ ወገኖች፣ የጌታችንን ቃል ለመለወጥ ወይም ለማሻሻል መሞከራቸው ነውና በጥብቅ እንቃወማለን።

## ጥያቄ፦ከቅዱስ ቊርባን ሌላ፣ «መስዋዕት ብለን» ለእግዚአብሔር የምናቀርበው ነገር አለ?

አዎን አለ፤ይኸም በንጹህ ልብ ሆነን በአንደበታችን የምናቀርበው ምስጋና የምስጋና መስዋዕት ይባላል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለዕብራውያን ክርስቲያኖች በጻፈው መልእክቱ፣ « እንግ ዲህ በስሙ የምናምን የአንደበታችን (የከንፈሮቻችን) ፍሬ የሆነውን የምስጋና መስዋዕት ዘወት ር ለእግዚአብሔር ማቅረብ ይገባናል» ሲል አስተምሮአል (ዕብ.፲፫፡ ፲፭-፲፮)። ቅዱሳን መላእክ ት ከኪሩቤልና ከሱራፌል ጋር ዘወትር ባለማቋረጥ ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት ምስጋና መስ ዋዕተ ስብሓት (የምስጋና መስዋዕት) ይባላል። ድሆችን መርዳትና መንከባከብም እግዚአብሔርን ደስ ስለሚያሰኘው መስዋዕት ይባላል (ዕብ.፲፫፡ ፲፮)።

ቅዱስ ቊርባንን ከመቀበል በፊት የሚነበብ የእምነት ቃል፦

አምናለሁ፤ አምናለሁ፤ አምናለሁ፤ እስከ መጨረሻይቱ እስትንፋስ እታመናለሁ፤ በሁለት ወገን ድንግል ከምትሆን ከሁላችን እመቤት ከቅድስት ድንግል ማርያም የነሣው የጌታችንና የአምላካ ችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋው ደሙ ይህ እንደሆነ፤ ያለመቀላቀልና ያለመጨ መር ፣ ያለመለወጥና ያለመለየት ከመለኮቱ ጋር አንድ ያደረገው፣ በጴንጤናዊ ጲላጦስ ዘመን ባ ማገረ ምስክርነት ምስክር የሆነ፣ስለ እኛና ስለ ሁላችንም ሕይወት አሳልፎ የሰጠው። አሜን። አምናለሁ፤ አምናለሁ፤ አምናለሁ፤ መለኮቱ ከሰውነቱ እንደ ዓይን ጥቅሻ ያህል እንኳን እንዳልተ ለየ እታመናለሁ፤ ማስተስረያ ይሆን ዘንድ አምነው ለሚቀበሉ ሁሉ አሳልፎ ሰጠው እንጂ። አሜ ን።

አምናለሁ፤ አምናለሁ፤ አምናለሁ፤ የጌታችን የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋው ደሙ ይህ እንደ ሆነ እታመናለሁ። ቸር ከሚሆን ከሰማያዊ አባቱ ጋር ማሕየዊ ከሚሆን ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ክብርና ምስጋና፣ ስግደትም፣ የሚገባው ይህ ነው፤ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለ ሙ አሜን። (የሐዋርያት ቅዳሴ፣ ቊ. ፻፩-፻፫)

ትምህርተ ሃይማኖት ኦርቶዶክሳዊት ከሚለው አቡነ ገብርኤል በ1991 ካሳተሙት የተወሰደ።